የዩኤስ የፍትሕ ሚኒስቴር
የኢሚግራንት እና የሰራተኞች መብት ጉዳይ ክፍል
የሲቪል መብቶች መምሪያ

# ለስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ስለ Form I-9 የተሰጠ መረጃ

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ስራ የሚጀምር ማንኛውም ሰው Form I-9 (ቅጽ I-9) መሙላት ያለበት ሲሆን ይህ በመንግስት የተዘጋጀ ቅጽ አሰሪዎች የእርስዎን ማንነትና ስራ ለመስራት የተፈቀደልዎ መሆኑን ለማጣራት ይጠቀሙበታል። የዚህ በራሪ ወረቀት ዓላማም እናንተ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች Form I-9 እንድትሞሉ ለማገዝና በዚህ ሒደት ውስጥ ያላችሁን መብት እንድታውቁ ለማገዝ ነው። በዚህ ሒደተ ውስጥ በዜግነትዎ ወይም በመጡበት ሃገር ማንነት ላይ ተመስርተው አድልዎ የሚፈጽሙ አሰሪዎች የኢሚግሬሽንና የዜግነት ሕጉን እየጣሱ ነው። ይህ ፀረ አድልዎ የሆነ ሕግ 8 U.S.C. § 1324b ላይ የሚገኝ ሲሆን የዚህ ሕግ ደንቦች ደግሞ 28 C.F.R. Part 44 (28 C.F.R. ክፍል 44) ላይ ይገኛሉ።

### ለ Form I-9 ክፍል 1 ራስዎን በተመለከተ መረጃ ይሰጣሉ።

በክፍል 1 ውስጥ ስምዎትንና እርስዎን የሚመለከቱ ሌሎች መረጃዎችን ይጻፉ። ይህን ክፍል ለመሙላት የሌላ ሰው እገዛ መጠየቅ ይችላሉ። ስራ ለመስራት ፈቃድ ያለዎት መሆኑን የሚገልጸው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች “ለመስራት የተፈቀደላቸው የውጭ ዜጎች” ስለሚባሉ እዚህኛው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። ከዚህ ሳጥን አጠገብ የስራ ፈቃድዎ የሚያበቃበት ቀን የሚጻፍበት ቦታ አለ። የስራ ፈቃድዎ ቋሚ በመሆኑ የፈቃዱ ማብቂያ ቀን መጻፊያ ቦታ ላይ “N/A” (ወይም “Not Applicable”) ብለው ይጻፉ። ክፍል 1 እንዴት እንደሚሞላ ተጨማሪ መረጃዎችን ከ Form I-9 instructions (የ I-9 መመሪያዎች ይሙሉ) ያንብቡ ወይም ለ Immigrant and Employee Rights Section (IER) (የስደተኛ እና ሰራተኛ መብቶች ክፍል) ወይም U.S. Citizenship and Immigration Services (USCIS) (የአሜሪካ ዜግነት እና ኢሚግሬሽን አገልግሎት) ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።

### ለ Form I-9 ክፍል 2፣ ማንነትዎንና የስራ ፈቃድዎን የሚያሳዩ ሰነዶች ለአሰሪዎ ማቅረብ አለብዎ።

Form I-9 ሶስት ዓይነት የሰነድ ዝርዝሮች አሉት–List A (ዝርዝር ኤ) (ማንነትዎንና የስራ ፈቃድዎን የሚያሳዩ ሰነዶች)፣ List B (ዝርዝር ለ) (ማንነትዎን የሚያሳዩ ሰነዶች) እና List C (ዝርዝር ሐ) (የስራ ፈቃድዎን የሚያሳዩ ሰነዶች)። በ List A የተጠቀሰውን ሰነድ ወይም List B እና List C ሰነዶችን በአንድ ላይ ለአሰሪዎ ማሳየት አለብዎ።

Form I-9 instructions እና regulations (የ I-9 መመሪያዎች እና ደንቦች ይሙሉ) የሚለው ውስጥ እንደ ደረሰኝ ያሉ አንዳንድ ሰነዶች የቆይታ ጊዜዎን ለማረጋገጥ በ Form I-9 ተቀባይነት አላቸው። በ Form I-9 ላይ የሚጠየቁ ሰነዶችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ለ IER ወይም USCIS ማሳወቅና በ 8 U.S.C. § 1324a(b)(1)(A) ላይ ማግኘት ይችላሉ።

ለማሳየት የሚፈልጉትን ትክክለኛ ሰነድ የመምረጥ መብት አለዎት። ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በመሆንዎ ምክንያት ብቻ ወይም በመጡበት ሃገር ምንነት ላይ ተመስርቶ አሰሪዎ የተወሰኑ ሰነዶችን እንዲያሳዩ ሊጠይቅዎት አይችልም፤ የተወሰኑ ሰነዶች እንዲቀርቡለት የሚጠይቅ አሰሪ ሕጉን በመጣስ አድልዎ እየፈጸመ ሊሆን ይችላል። ይህ የሕጉ ክፍል በ 8 U.S.C. § 1324b(a)(6) ላይ ይገኛል። ለምሳሌ፣ እርስዎ ስራ እንዲሰሩ የተሰጠዎ ፈቃድ፣ I-766 (EAD) ቢኖርዎትም የግዛት መታወቂያ (የList B ሰነድ) እና ያልተገደበ የማህበራዊ ዋስትና ካርድ (የList C ሰነድ) የመሳሰሉ ሌሎች ሰነዶችን ለማሳየት ሊወስኑ ይችላሉ። ሰነዶችን ለመምረጥ ያሉዎትን መብቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ከ IER ጠይቀው ማግኘት ይችላሉ።



## የተለያዩ ዓይነት የጸኑ የ Form I-9 ሰነዶች ሊኖሩዎት ይችላል።

ለ Form I-9 የ I-94 ሊያሳዩ ይችላሉ። የእርስዎን I-94 ካርድ ማግኘት ይችላሉ ወይም የእርስዎን I-94 ከ Customs and Border Protection (ጉምሩክና ድንበር ጥበቃ) ድረ ገጽ ማግኘት ይችላሉ።

ስደተኛ ከሆኑ፣ your I-94 is a receipt (የእርስዎ I-94 ደረሰኝ ነው) ለ List A ሰነድ በደረሰኝነት የሚያገለግል ሲሆን እርስዎ ስራ ከጀመሩበት ቀን አንስቶ ለ90 ቀናት ያገለግላል። ከ90 ቀናት በኋላ EAD ወይም የ List B ሰነድና ያልተገደበ የማህበራዊ ዋስትና ካርድን አብረው ማሳየት አለብዎ። የስደተኛ I-94 አጠቃቀምን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከ IER በመጠየቅና 8 C.F.R. 274a.2(b)(1)(vi)(C) ላይ በማንበብ ማግኘት ይቻላል።

ጥገኝነት ጠያቂ ከሆኑ፣ የእርስዎን I-94 የማለቂያ ጊዜ የሌለው a permanent List C document (ቋሚ የ List C ሰነድ) አድርገው መጠቀም ይችላሉ።

ጥገኝነት ጠያቂዎችና ስደተኞች ለ EADs ብቁ ናቸው። የእርስዎ EAD የአገልግሎት ዘመኑ ቢያበቃም እርስዎ EAD እንዲታደስልዎት አመልክተው ከሆነ፣ አሁን ባለዎት EAD መስራት መቀጠል ይችላሉ። የእርስዎ EAD የአገልግሎት ዘመኑ ካበቃ በኋላ ላሉት 180 ቀናት EAD ከ I-797C መቀበያ ደረሰኝ ጋር አብረው ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ይህም ደረሰኝ መንግስት የእርስዎን የ EAD የእድሳት ማመልከቻ መቀበሉን የሚያሳይ ነው። ለተጨማሪ መረጃ ለ IER ይደውሉ።

ከሁለት ቀናት በላይ ለሚቆዩ ስራዎች lost, damaged or stolen (የጠፉ፣ የተጎዱ ወይም የተሰረቁ) ሰነዶችን ደረሰኝ ማሳየት ይችላሉ።

Form I-9 ለመሙላት ሰነድዎን አንዴ ካሳዩ፣ አሰሪው በድጋሚ ሰነዶችን እንዲጠይቅዎት የሚፈቀድለት በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ነው። አንድ አሰሪ ሰነዶችን በድጋሚ መጠየቅ የሚችልባቸው ደንቦች Handbook for Employers (የአሰሪዎች መረጃ ሰነድ) ላይ በዝርዝር የቀረበ ሲሆን በ 8 C.F.R. 274a.2(b)(1)(vii) ላይም ይገኛል።

የእርስዎን EAD ለክፍል 2 ካሳዩ፣ አሰሪዎ የ Form I-9 ክፍል 3ን ለመሙላት ሌላ ሰነድ እንዲቀርብለት የሚጠይቀው የእርስዎ EAD የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ ነው። ያልተገደበ የማሕበራዊ ዋስትና ካርድን የመሳሰሉ የጸና የ List A ወይም የ List C ሰነድ ማቅረብ ሊፈልጉ ይችላሉ። አዲስ EAD ለማሳየት ቢወስኑም ይህን ለማድረግ አይገደዱም።

የእርስዎን EAD ለክፍል 2 ካሳዩ፣ አሰሪዎ የ Form I-9 ክፍል 3ን ለመሙላት ሌላ ሰነድ እንዲቀርብለት የሚጠይቀው የእርስዎ EAD የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ ነው። ያልተገደበ የማሕበራዊ ዋስትና ካርድን የመሳሰሉ የጸና የ List A ወይም የ List C ሰነድ ማቅረብ ሊፈልጉ ይችላሉ። አዲስ EAD ለማሳየት ቢወስኑም ይህን ለማድረግ አይገደዱም።

የስራ ፈቃድ እንዳለዎት ለማስረዳት ለክፍል 2 ያልተገደበ የማህበራዊ ዋስትና ካርድ ካሳዩና የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ የሚለው ላይ “N/A” ብለው በክፍል 1 ውስጥ “ለመስራት የተፈቀደለት የውጭ ዜጋ” የሚለው አጠገብ ላይ ከጻፉ፣ አሰሪዎ ሰነዶችዎትን በድጋሚ ማየት አያስፈልገውም። አስፈላጊ ባልሆነ ሁኔታ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በመሆንዎ ምክንያት ብቻ ወይም በመጡበት ሃገር ምንነት ላይ ተመስርተው ሰነዶችን የሚጠይቁ አሰሪዎች የሕግ ጥሰት እየፈጸሙ ሊሆን ይችላል። ይህን የሕጉን ክፍል በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከ IER በመጠየቅ ወይም ከ at 8 U.S.C. § 1324b(a)(1) ወይም (a)(6) ማየት ይችላሉ።

## ስራ መስራት ለመጀመር የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር አያስፈልግዎትም።

ስራ አግኝተው (SSN) የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር ከሌለዎት፣ ሰራተኞች የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር እስከሚሰጣቸው ድረስ ስራ ለመስራት እንደሚችሉ Social Security Administration (የማሕበራዊ ዋስትና ባለስልጣን) ለአሰሪዎች መመሪያ ይሰጣል።

የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን በመጠባበቅ ላይ እያሉ ቢሆንም ለሰሩት ስራ አሰሪዎ ክፍያ ሊፈጽምልዎት ይገባል። በ29 U.S.C. § 201 ላይ የሚገኘው የፍትሐዊ የሰራተኞች ስታንዳርድ ሕግ እርስዎ ለሰሩት ስራ ሁሉ ክፍያ የማግኘት መብት ይሰጥዎታል።

ስራ በሚጀምሩበት ወቅት የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር ከሌለዎት፣ በክፍል 1 ውስጥ የሚገኘውን የ SSN ሳጥን ክፍት ይተውት። አሰሪዎ E-Verify ቢጠቀምም እንኳን ይህን ማድረግ አለብዎት።

የኢሚግራንት እና የሰራተኞች መብት ጉዳይ ክፍል

1-800-255-7688

ማንነትዎን ሳይገልጹ መደወል ይችላሉ። የቋንቋ አገልግሎት እናቀርባለን።

www.justice.gov/ier

1-800-237-2515 TTY

ይህ በራሪ ወረቀት የመጨረሻ የኤጀንሲ እርምጃ አይደለም፣ ሕጋዊ አስገዳጅነት የለውም፣ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረትም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሳኔ ሊሻር ወይም ሊሻሻል ይችላል። ይህ በራሪ ወረቀት አግባብነት ባለው አዋጅ፣ ደንብ ወይም የቀድሞ የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ከተቀመጠው ያለፈ ሕጋዊ ግዴታና ሃላፊነትን አያስቀምጥም።